ቁጥር፡-............................

ቀን፡-23/04/2012 ዓ.ም

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ  የምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ እና የቅዱስ ሲኖዶስ አባል።

ጉዳዩ፡- <u>የነቢያትን ጾም መግቢያ እና በዘመነ ዮሐንስ የልደትን በዓል  ስለማስረዳት ይሆናል</u>

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እና ሀገራችን ኢትዮጵያ በሕገ ልቡና፣ በህገ ኦሪት፣ በሕገ ወንጌል በአጠቃላይ በሦስቱም ሕገጋት እግዚአብሔርን ስታመልክ የኖረች ሀገር ናት። ወደፊትም ትቀጥላለች።

የሃይማኖት መሠረቷም ለነቢያት የተገለጠው በሐዋርያት የተሰበከው በመላእክት የታወቀው መድኅነ ዓለም ክርስቶስ ነው።

ይኸውም ሃይማኖታችን  አስቀድሞ ለአበው የተገለጠ እና እኛም የተቀበልነው ነው እንጂ ጊዜ አመጣሽ ሰው ሠራሽ አይደለም።

ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለ ተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ እና የመከርኋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ እንዲል ይሁ 1፣3።ትምህርቱም በክርስቶስ ተሰብኮ በሐዋርያት ዳብሮ በሊቃውንት ተተርጎሞ የምናገኘው ነው። ስለዚህም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን  በመሥዋዕት እና በክህነት በሐዋርያዊ አምልኮት የታጀበች ሐዋርያዊት፣ ቅድስት፣ ዕንተ ላዕለ ኲሉ ናት።

በዚህም ከሐዋርያት ሲያያዝ ያለ ተመትሮ (ያለመቋረጥ) የመጣ ሲኖዶሳዊ ሰንሰለት እና የጠበቀ መዋቅር አላት።

ስለሆነም በሃይማኖት የማይመስላትን እና የሚቃወማትን የመለየት እና ቀኖና የመስጠት ሥልጣን ገንዘቧ ነው።

ከዚህ የተነሳም ሦስቱን ታላላቅ ዓለም አቀፍ ጉባኤያትን ጉባኤ ኒቅያን ፣ጉባኤ ቁስጥንጥንያ፣ ጉባኤ ኤፌሶን ተቀብላለች በዚህ ውሳኔዋም ዛሬ የምናያትን ቤተ ክርስቲያን ያለመለወጥ ለመረከብ ችለናል ።

ነገር ግን ከፈተና እና ከችግር ግን ጨርሳ አልተላቀቀችም።ምክንያቱም በባህር ላይ ያለች መርከብ ናት እና ።

<<ደግሞመንግሥተ ሰማያት ወደ ባሕር የተጣለች ከሁሉም ዓይነት የሰበሰበች መረብን ትመስላለች>> እንዲል ማቴ 13፣47

ስለሆም ኢትዮጵያ ሀገራችን እና ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በ 8 ኛው ክፍለ ዘመን በጉዲት። በ 15 ኛው ክፍለ ዘመን በግራኝ አህመድ ጽኑ መከራን ተቀብላለች ።

ከግራኝ በኋላም ካቶሊካውያን (ኢየሱሳውያን ) ውሥጥ ለውስጥ ሰርገው በመግባት ያስቸግሩ ነበር ። በተለይም በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት በጉባኤ ከተረቱ በኋላ እርስ በርሳችን እንድንከፋፈል እነ እልፎንሱ ሞንዴዝ ለቆረንጭ ተክለሃይማኖት እና ለመናፍቅ ኤዎስጣቴዎስ የቅባት እና የጸጋን ባህል በማስተማር ያደረሱት ተጽእኖ ቀላል አይደለም ለቀላል ማስረጃም የአጼሱስንዮስን ዘመን ማየት ይቻላል።

ስለሆነም ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ባላወቁት ሴራ ያንዲት እናት ልጆች ቢሆኑም የኢየሱሳውያን ተንኮል ልዩነትን ሳይፈጥርባቸው ያለፈ ግን አልነበረም።

ይኸውም ሲያያዝ የመጣው የሚሲዮናውያን ተንኮል ዛሬ ድረስ የልዩነት ምልክቶችን ሲያንጸባርቅ ይስተዋላል። አንዳንድ ጊዜም ቀኖና እና ዶግማ (ዶክትሪን) በማምታታት ምእመናን ሲያወናብድ ይስተዋላል። በተለይም የቅዱስ ሲኖዶስን ቀኖናን የመወሰን ልዕልናን እና ድርሻን ይጋፋል።

ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን የመንፈስ ቅዱስ ልጆቹ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የቀኖና ባለቤት እና በበጎው ነገርሁሉ የከበረች ናት ።ስለሆነም ከሰብዓቱ አጽዋማት አንዱ የሆነው ጾመ ነቢያት ሲሆን የሚገባው በአራቱም (ወንጌላውያን)ዘመናት ሁል ጊዜም ባለመቀያየር ኅዳር 15 ቀን ብቻ ነው። በዘመነ ዮሐንስም ቢሆን አይለወጥም።ምክንያቱም፡-

1 ኛ በሲኖዶስ እና በፍትሀ ነገሥት እንደተወሰነው ቀኖናን የመሥራት ስልጣን ለቅዱስ ሲኖዶስ ስላለው ነው።

- ወለእመ ኮነ ዘአህጸጽነ ምንተኒ እምነ ግብር ፍትሁ አንትሙ በዘይደሉ “ከሥራ ሁሉ ያጎደልነው ምንም ነገር ቢኖር እንደሚገባ እናንተ ፍረዱ”
- እስመ ብነ ለኵልነ መንፈስ እግዚአብሔር “የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በሁላችን ላይ አድሮብናልና”
- ወለእመ ተርፈ እምኔነ ያዘክር ኤጲስቆጶስ “ከእኛ የቀረ ቢኖር ኤጲስጶጶሱ ይሙላው”

- ወለእመ ተርፈ እምኔነ ምንትኒ ኦ ፍቁራን ለዝንቱሂ ይከስቶ እግዚአብሔር ለዘኮነ ድልዎ "ወዳጆች ሆይ ከእኛ ምንም ምን የቀረ ቢኖር ለሚገባው ሰው እግዚአብሔር ይግለጠው"
- ወትትመራህ ቤተ ክርስቲያን በዘይደሉ ኀበ መርሶ ወዛህን "ቤተ ክርስቲያንም እንደሚገባ ወደ እረፍት ወደብ ትመራ" መቅ፣ጉባ.ገጽ 14
- ዘአሰርክሙ በምድር ይኩን እሱረ በሰማያት ወዘፈታህክሙ በዲበ ምድር ይኩን ፍቱሀ በሰማያት "በምድር ያሰራችሁት በሰማይ የታሰረ ይሁን በምድር የፈታችሁት በሰማይ የተፈታ ይሁን" ማቴ 18፣18
- ወናሁ ፈጽምነ ለክሙ ትምህርተ ዘንጉበክሙ በእንተ ትንሣኤ ሥጋ ወዘተርፈ ከማሁ ጽሑፍ ወለእመ ቦ ዘተርፈ ምንተሂ ይደሉ ዘክሮቱ ወይዜክሮ ኤጲስቆጶስ "እነሆ ስለ ስጋ ትንሣኤ የምንሰጣችሁን ትምህርት ፈጸምነ  ከመጻፍ የቀረው ግን ሊያስታውሱት ይገባል ኤጴስስቆጶስ ይሙላው" ሲኖገጽ 26
- ወለእመ ቦ ዘሀደግነ ንህነ ፍትሁ በዘይደሉ እስመ ኩልነ መንፈስ እግዚአብሔር ብነ "እኛ ያስቀረነው ቢኖር እናንተ እንደሚገባ ፍረዱ ለሁላችን መንፈስ ቅዱስ አለን እና" ሲኖ.ገጽ 20 ይላል
- ይህን ቃል ይዞ ቅዱስ ሲኖዶስ የመወሰን ድርሻ አለው ።

2 ኛ በፍትሐነገሥትም ሆነ በሥንክሳር የነቢያት ጾም መግቢያ ኀዳር 15 ቀን እንደሆነ ይናገራል።

- ወውእቱ ጾም ዘይቀድም እምልደት ወጥንተ ዚአሁ መንፈቀ ኀዳር ወፋሲካሁ በዓለ ልደት "ይህም ጾም ከልደት የሚቀድም መጀመሪያው ኀዳር 15  ፋሲካውም የልደት በአል ነው" ፍት.ነገ.አን.15፣568
- እመ ይትከሀልክሙ ፈድፋደ እምዝንቱ ጹሙ ወለእመሰ መጽአ በእንቲአሁ ተጋእዞ ጸዊሞቱ ድልው ወይሄይስ ፈድፋደ እሙብልእ "የሚቻላችሁስ ከዚህ አብዝታችሁ ጹሙ በጾም ምክንያት ክርክር የሚሆን ከሆነ ግን ከሙብላት መጾም እጅግ ይሻላለል" ፍት. ነገ.አን 15፥584
- ወበዛቲ ዕለት ጥንተ ጾመ ጌና ዘውእቱ ልደቱ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ሎቱ ስብሐት ዘሠርእዎ ክርስቲያን ያዕቆባውያን ዘግብጽ ሳህሉ ወምህረቱ "በዚህችም ዕለት የጌና ጾም መጀመሪያ ነው ።ይኸውም ክብር ይግባውና የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በግብጽ የሚኖሩ ያዕቆባውያን ክርስቲያኖች የሠሩት። ይቅርታው ቸርነቱ ለሁላችን ይሁንልን ይደረግልን አሜን" ስንክሳር ኀዳር 15
  እንዲል።

3 ኛ፡- ቅዱስ ሲኖዶስ በ 1980 በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት  ዘመነ ፐትርክና ጊዜ ስለወሰነ ነው። ስለዚህ ጾሙ ሁል ጊዜም ያለተፋልሶ ኀዳር 15 ቀን ብቻ ነው።

- ከዚህ ወጥቶ መጋፋት ግን

1 ኛ. ቀኖና እና ዶክትሪንን(ዶግማ) ያለመለየት ችግር ነው።

2 ኛ. የቅዱስ ሲኖዶስን የውሳኔ ልዕልና መጋፋት ይሆናል።

3 ኛ. የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔን ሳናከብር ቀኖናዊት ቤተ ክርስቲያን አለችን ማለትም አይቻልም።

4 ኛ. ይህን ካላከበርን የመወሰን ድርሻውስ ለማን ሊሆን ነው? ለግለሰብ ወይስ የቅዱስ ሲኖዶስ።?

- ልደት

➢ 1 ኛ፡- በዓለ ልደት መቸ ይውላል ቢባል  በአራቱ ወንጌላውያን ማለትም በዘመነ ማቴወስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ፣ ሁል ጊዜም ታኅሣስ 29 ቀን ይውላል።

➢ በዘመነ ዮሐንስ ግን በ 28 ቀን ይውላል፡ ምክንያቱም፡-1 ኛ በዓለ አብሳሬ፣ በዐለ ተበሳሪ፣ በዐለ መበስር አለ በአለ አብሣሪ የቅዱስ ገብርኤል ነው፡ በታህሳስ 22 ይከበርለታል። በአለ መበስር  ባለቤቱ ክርስቶስ ነው። ስለሆነም ለበአለ መበሥር ለክርስቶስ  በሦስቱም ወንጌላውያን ይከበርለታል። በዓለ ተበሣሪ የእመቤታችን ነው።  በዘመነ ዮሐንስ እመቤታችን ሲሶ ሲሶ አላት እና መታሰቢያነቱ ለእመቤታችን ነው። በዓሉም በዓለ ጌና ይባላል ጌና ማለት በዳውሮኛ ቋንቋ እመቤት ማለት ነው።ርስት አንቲ ወስሉጥ ስምኪ በኀበ እግዚአብሔር ፡-በእግዚአብሔር ዘንድ ሲሶ ሲሶ ያላት ርስት  አንቺ ነሽ እንዲል  ቅዳሴ ሕርያቆስ።

➢ የልደት ቃለ እግዚአብሔርም በስፋት የሚባለው እመቤታችንን የተመለከተ ነው።

2 ኛ ለቀዳማዊ ልደቱ መታሰቢያ ሊሆን ለቅዱሳን ሁለት የባህርይ ልደት የላቸውም ስለዚህም ሁለት ጊዜ ልደታቸው አይከበርላቸውም ለእርሱ ግን ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት አንድ ለደት ድኅረ ዓለም ከድንግል ማርያም ያለአባት አንድ ልደት፡-ሁለት ልደት አለው እና በሦስቱ ወንጌላውያን መድራዊ ልደቱ በዘመነ ዮሐንስ ግን ሰማያዊ ልደቱን በማሰብ እናከብራለን ምክንያቱን ሰማያዊ ልደቱ የታወቀው በምድራዊ ልደቱ ነውና።

➢ ወዓዲ ይደልወነ ንእመን ከመ ቦቱ ለወልደ እግዚአብሔር ክልኤቱ ልደታት ዳግመኛም ለወልደ እግዚአብሔር ሁለት ልደት እንዳለው ልናምን ይገባናል። እንዲል። ሃይ.ባስ 34፣6 ከዚህ የተነሣም በአማኑኤል ግዕዝ ዋዜማ፣ግዕዝ ኪዳን ይባላል ግዕዝ የአብ ምሳሌ ስለሆነ ነው።

3 ኛ ቅዱስ ያሬድም ቀለም እና ለእመ ኮነ መዝሙር ይሠራለታል በአለ ልደት በ 28 ባይውል ኑሮ ግን  ባልሰራለትም ነበር።

4 ኛ የጌታ ጽንሱ እንዳይፋለስ ነው። የዘመን ቁጥር ስለ ሚያደርስ ከዮሐንስ መጨረሻ እስከ ዮሐንስ መግቢያ ዓውደ ዓመት ትርፋ 24 ሰዓት ሞልቶለት የሚገባው ከምሽቱ ነው። ስለሆነም ጳጉሜን 6 ቀን ስለምትሆን ልደት በ 28 ቀን ይውላል ይህችውም እለተ ምርያ ናት(የድኅነት ቀን) 2 ቆሮ 6፣2።እንኪያ የቅዱሳን በዓላት ስለምን አይፋለሱም ቢባል በኩረ በአል ልደትን በክብር ካስታወስነ  የቅዱሳን ልደት በዚሁ ይጠቃለላል ተብሎ ነው።

በዓላትም በታህታይ ዕለት ነው የሚውሉት ማለትም እንደሌሎች ዕለታት ሁለት ቀን ሰግር አያደርጉም።

5ኛ. አመ እስራ ወሰሙኑ በአለ ጌና ታኅሣስ 28 ቀንም የጌና በዓል ነው
መቅድመ ተአምር
ልደት በዘመነ ዮሐንስ በ28 ቀን እንደ ሚውል ስለሚነግረን ነው።
ስንክሳርም፡-
እስመ አበዊነ መምህራነ ቤተ ክርስቲያን ወበዛቲ ዕለት ተሰነአዉ በምክሮሙ ከመ ይግበሩ በአለ ልደት ቅድስት በክልኤቱ ዕለታት፡

አባቶቻችን የቅድስት ቤተ ክረስቲያን መምህራን በዚህች ዕለት ቅድስት የምትሆን የልደትን በአል በሁለቱ ዕለታት እንዲያከብሩ ተስማሙ። እዚህ ላይ በሁለቱ ዕለታት ሲል በሦስቱ ወንጌላውያን ማለትም በቅዱስ ማቴዎስ፣ በማርቆስ እና በሉቃስ በ29 በዘመነ ዮሐንስ ደግሞ በ28 በዓለ ልደት ይከበራል ማለት ነው እንጅ በአንድ ዓመት ላይ በ29 እና በ28 ቀን ይከበራል ማለት አይደለም።
ስንክሳር ታኅሣስ 29 ስለሚል ነው።

6ኛ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ቀኖና ስለሚያዝ ነው።
ነገር ግን

ባንዳንድ በመጽሔት እና በትራክ በአፍ በንግር ተገቢ ያልሆነ ትምህርት የሚያሠራጩ አካላት ግን ከአበው መምህራን ያልሰሙትን ከመጻሕፍት ያላገኙትን በትውፊት ያልተቀበሉትን የግል ልዩ ሀሳባቸውን እየያዙ ምእመናን ማምታታት አይገባም። ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን የሚቃወም እና የመወሰን ድርሻዋን የሚጋፋ ስለሆነ ነው።

በ2008 ዓ.ም.

በሊቀ ማእምራን ብርሃነ መስቀል አጠና በተባሉ ግለ ሰው ዜና ቤተ ክርስቲያን ዘኢትዮጵያ በተባለ ጋዜጣ ላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዓለ ልደትን ታኅሣስ 28 ቀን በ4 ዓመት አንድ ጊዜ በዘመነ ዮሐንስ ስታከብር ስህተት ነው ብለው ይከሳሉ ባስረጅ ያቀረቧቸው (የጠቀሷቸው) ጥቅሶች ግን ገዥ አይደሉም።

እነሱም **1**ኛ ጥያቄ

ጳጉሜን 6 የምትሆነው በዘመነ ሉቃስ ነው በዓለ ልደት በ28 የሚውለው ደግሞ በዘመነ ዮሐንስ ነው። ይኸውም ሁለቱ ምንም ግንኙነት የላቸውም ብለዋል። ነገር ግን ይህን ሀሳብ ስናየው ትክክል አደለም፡-

1 ኛ የዕለተ ምርያን ሰግርነት አለመረዳት ነው ምክንያቱም እለተ ምርያ ጳጉሜን 6 በዋለበት ቀን እለተ ልደት ትውላለች፤ በመሠረቱ ዕለተ ምርያ በምትውልበት በአራቱም ወንጌላውያን ቀኗ አይለውጥም።

እለተ ምርያ ማለት እለተ ሠግር ዕለተ መድኃኒት ማለት ነውና።

ዕለተ መድኃኒት ማለትም ዕለተ ልደት ነው።

2. ወንጌለዊ ለወንጌላዊ ሰዓትና ኬክሮስን ያስረክባል እንጂ በኔ ብቻ ይቅር አይልም ስለዚህም በሉቃስ ያለው ተረፈ ዓመት ከሌሎች ወንጌላውያን ጋር በመደመር በአራተኛው ዓመት አንድ ሙሉ ቀን ስለሚሆን ይህንንም ዮሐንስ ስለሚረከበው በዓላት አንድ አንድ ቀን በማጉደል ሰግር እያደረጉ ይታያሉ።

ልደትም በኩረ በአልነውና በ 28 ቀን ይውላል እንጂ 29 ኙን አይነካም

3. ዕለተ ጽንስን ማፋለስ (ማቃወስ)ይሆናል ከመጋቢት 29 ቀን ጀምሮ እስከ ታኅሣስ 29 ቀን ቢቆጥሩ በሦስቱም ወንጌላውያን 9 ወር ከ 5 ቀን ይሆናል በዘመነ ዮሐንስ ግን 9 ወር ከ 6 ቀን ይሆናል፤ ስለዚህ በዘመነ ዮሐንስ ልደት የሚውለው በ 28 ቀን ነው እንጂ በ 29 ቀን አይደለም ያ ከሆነ ግን እለተ ጽንስን ያፋልሳል።

4 ኛ፡- በአራት ዓመቱ በ 28 ቀን የሚውለው ቀዳማዊ ልደቱን ለማስታስ(ለማዘከር) ስለሆነ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ያዝዛል ቀኖናን የማውጣት መብቱ ደግሞ የቅዱስ ሲኖዶስ ነው እንጂ የግለ ሰብእ አይደለም።

2 ኛ. ጥያቄ፡- ጳጉሜን 6 ስትሆን በዓለ ልደት ቦታውን ይለቃል ከተባለ ግዝረቱም ጥምቀቱም ቃና ዘገሊላ እና ልደተ ስምኦንም እና ሌሎች በአላትም ቦታቸውን ይለቁ ነበር እውነቱን የተከተለ ቀጥተኛ በቤተ ክርስቲያን ስሌት ቢሆን ኑሮ።

ይህም ቢሆን ያለመረዳት ችግር ካልሆነ በስተቀር ልደት በ 28 ቀን እንዳይውል ምክንያት ሊሆን አይችልም ምክንያቱም፡-

1 ኛ በዘመነ ዮሐንስ ሁሉም በዓላት በዘመነ ሉቃስ ከዋሉበት ቀን ሰግር የሚያደርጉት አንድ አንድ ቀን ነው በሌሎች ወንጌላውያን ዕለታት ግን ሁለት ሁለት ቀን ነው። ይህም ልደት በ 28 ቀን እንዲውል ያሳየናል።

2ኛ በኩረ በዓላት የሆነውን የልደትን ቀን በትክክል ካከበርን የሌሎች መክበር በእርሱ ልደት ነውና የግድ አሳሳቢ ሊሆን አይችልም።

በዚኸውም ላይ ሰግር አላደረጉም ሊባል አይችልም ምክንያቱም ዕለታቸውን እየለቀቁ የሚውሉ ስለሆነ።

3ኛ ከላይ እንደተናገርነው የቀኖናን (የሥርዓትን)ጉዳይ አለመረዳት ነው ቅዱስ ሲኖዶስ የተስማማበትን መቃወም ራስን መልዕልተ ሲኖዶስ (ከሲኖዶስ በላይ)ማድረግ ነው ።

4ኛ በበዓላት ተፋልሶ ያመጣል የሚባለው ግን ስህተት ነው። ምክንያቱም ከመጻህፍትም አላገኘነውም ከመምህራንም አልሰማነውም። ከአበው ያገኘነውን ተቀብለን እናከብራለን እንጂ እንግዳ ትምህርት ማስተናገድ አይገባማንም ልደተ ስምዖንን ሆነ ሌሎችን በዓላት ባሉበት እንጂ በሰግር እንደ ሚውሉ አልተጻፈልንም።

ይህ ከሆነም የቅዱስ ሲኖዶስ የመወሰን ድርሻ እንዴት ሊገኝ ይችላል።በዚያውስ ላይ የቀኖና ባለቤት የሆነች ቤተ ክርስቲንስ እንዴት ልትኖረን ትችላለች።

3ኛ ጥያቄ፡- ቅዱስ ያሬድ ለበዓላት ሁሉ ለእመኮነ ሲሰራ ለዚህም ይሰራለት ነበር ለሚለው ይህ አባባል በትክክል የቅዱስ ያሬድን የዜማ ይትበህል አለመረዳት ነው እንጂ ስንኳን ለእመኮነ መዝሙር ይቅር እና ክብረ በዓል ይሠራለት የለም ወይ። መዝሙሩም ወእንዘ ሀለው ነው።ለመሆኑ ይህ በቂ ማስረጃ ነው? ቤተ ክርስቲያን ቀኖናን ሠራች እንጂ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን አልሠራትም ያማ ቢሆን ዕንተ ላዕለ ኵሉ መባል ወዴት በተገኘ ነበር።

4ኛ ጥያቄ፡- በዘመነ ዮሐንስ ታኅሣስ 28 ቀን ይከበር የሚሉ ማስረጃቸው አንድ መጽሐፈ ስንክሳር ብቻ ነው ይኸውም አባ ዘገየ የተባሉ አባት ከግራኝ ወዲህ የተጻፈ ስንክሳር እንጂ ከዚያ በፊት የነበረ ስንክሳር በ28 አክብሩ አይልም ሲሉ በመድበለ መጽሐፋቸው ጽፈዋል

ለማስጃም የ3 አብያተ ክርሰቲያናት የጎንደር ደብረ ብርሃን ሥላሴን፣የመህልጌ ጊየርጊስን እና የታች ጋይንት ስንክሳሮችን ጠቅሰዋል። ብለው ለተናገሩት

1ኛ. ልደት በ28 ቀን እንዲከበር ከግራኝ በፊት አልነበረም ለማለት የግለሰብ ማስታወሻ ከመጥቀስ የቤተክርስቲንን የቀኖና አንድነት መትቀስ አይሻልም ነበር? ግለ ሰብእ ብቻውን ለታላቋ ቤተ ክርስቲያን ማስረጃ ሊሆን ይችላልን?

2ኛ በመቅድመ ተአምር እንደተጻፈው ሁሉ በአጼ ዘርዐ ያእቆብ ዘመነ መንግሥት በ28 ቀን ይከበር እንደነበር በዘመኑ የተጻፈው መቀድመ ተአምር በታኅሣስ 28 ቀንም በአለ ጌና ነው ይለናል።

3ኛ ማስረጃ ሳይኖረው በቅዱስ ቅብብሎሽ የመጣችውን ቤተ ክርስቲያን መውቀስ  ትውፊት አልባ ማድረግ ነው።

4ኛ. ቀኖና(ሥርዓት )የሚወሰነው መቼ እና መቼ እንደሆነ አለመረዳት ነው ምክንያቱም ይህ ሥርዓት እንጂ ሃይማኖት አይደለም እና። ቅዱስ ሲኖዶስ እንደ ጊዜ ግብሩ የመወሰን ድርሻ አለው ለዚህም ከላይ ባየነው የፍትሀ ነገሥት እና የመጽሐፈ ሲኖዶስ  አንቀጾች መረዳት ይቻላል።

በእነ እከሌ ስንክሳር አለ የሚለው ግን ውሸት ነው እኛም ከቦታው ካሉመምህራን እንዳጣራነው ውሸት እንደሆነ ተረድተናል  አንዳንድ ቦታ ቄርሎስ እንዳለ ብለው የጠቀሱትን ስንፈልገው ከቄርሎስ መጽሐፍ ማግኘት አልቻልንም ያልተጻፈ ቄርሎስ ይኖራቸው እንደሆነ ግን አላወቅንም ።

ዳግመኛም

ዳግመኛም ልደት ስለጾመ ገሐድ የሚነሳ ሀሳብ አለ ጾመ ነቢያት መላው 44 ቀን ነው። በሦስቱ ወንጌላውያም ዘመናት ተፋልሶ የለበትም ።በዘመነ ዮሐንስ ግን ጾሙ 43 ቀን ብቻ ነው።  ይኸውም 40ው ነቢያት የጾሙት ሲሆን 3ቱ ግን ጾመ ፊልጶስ እና ጾመ አብርሃም ሶርያዊ  ናቸው። አንዱ ደግሞ ጾመ ገሐድ ናት ። በዘመነ ዮሐንስ ግን ጾመ ገሐድ ጾምን በጾም መደረብ ልማድ ስለሆነ ተደርቦ ይውላል። ማለትም ጾመ ድኅነት በሌሎች አጽዋማት ተደርቦ እንደሚውል ሁሉ ማለት ነው። ገሐድ ሁለት ቀን አይጾምም አንድ ገሐድ ነው እንጂ።

ማጠቃለያም

ቅዱስ ሲኖዶስ ወልደ አብ የተባለ የቅባት እና የጸጋን ኑፋቄ የሚያስፋፊ መጽሐፍን ባወገዘበት አንቀጽ በግንቦት ወር 2010 ዓ.ም በተራ ቁጥር 15 በተወያየበት አንቀጽ ውግዘቱን አስተላልፏል። ምንም እንኳን በጥንትም በአበው ሊቃውንት የተወገዘ  ካቶሊካዊ ትምህርት ቢሆንም ቅዱስ ሲኖዶስ አጽንኦቱን ሰጥቷል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንደ ግለ ሰብእ የቅባት ምንፍቅናን የያዘ ሊኖር ይችላል ቤተ ክርስቲያንን ግን አይወክልም ።የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንጂ የቅባት ቤተ ክርስቲያን የሚባል የለም።

“ጰንተን ሃይማኖታችንን እንጠብቅ”

“እግዚአብሔር ኢትዮጵያን እና ህዝቦቿን ይባርክ”